# “ … ተራራ ጫፍ ላይ ወጥቼ እያሰብኩ ነው …” (ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ)

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሞተበትንና የቆሰለበትን የነጻነት ትግል ለግል ሥልጣን ጥማቱ ለማዋል ያደረገው ሙከራ ስለከሸፈበት ዶክተር ብርሃኑን እንደ ድሮው በየጊዜው አንሰማም። አልፎ አልፎም ሲሰማ የንዴት የቁጭትና የዘለፋ ንግግር ነው የሚያዘንበው።

ሰሞኑን ባደረገው የተከታዮቹ ስብሰባ ላይ አገር ቤት ለምን እንደማይመለስ ለቀረበለት ጥሩ ጥያቄ ተገቢውን መልስ ከመስጠት ይልቅ ጥያቄው እንደማይገባውና እንደሚደንቀው፣ ይህንን የሚያስቡ ሰዎችም ራሳቸውን እየሰደቡ እንዳሉ በመግለጽ ከጉዳዩ ጋር ያልተዛመደ ሞላጫ መልስ ሰጥቷል። ቀጥሎም ባልሄድስ ? እናስ ? እናስ ባልሄድ ? በግድ ሂድ ነው እንዴ? በማለት ጥያቄውን አድፈንፍኖ ለማለፍ ሞክሯል። አሜሪካ መጥቶ ሥራ ለመያዝ ሬዚዩሜውን ለማሳመር ነበር እንዴ በምርጫ የተወዳደረው? ለማለት ተገደናል።

ከዚያም ሰለወደፊቱ ሲገልጽ በአሁን ሰዓት ለተከታዮቹ ምን ዓይነት አመራር መስጠት እንዳለበት እንደማያውቅ፣ በየትኛው አቅጣጫ መሄድ እንዳለበት ለማወቅ እንደተቸገረ ገልጾ የቀጠረው ዩኒቨርሲቲ በጣም ስለሚወደው ለሚከፈለው ደመወዝ እንኳ ሥራ መሥራት እንደሌለበትና እንደማይጠበቅበት ተናግሮ በአሁኑ ጊዜ ተራራ ጫፍ ላይ ወጥቶ እያሰበ መሆኑን ገልጿል። ለመሆኑ የትኛው ዩኒቨርሲቲ ይሆን ለማያስተምር መምህር ደመወዝ የሚከፍል ? ወይስ ዶክተሩ ከሌላ ምንጭ ገንዘብ ተቆራጭ ተደርጎለታል? ከሆነስ ምንና ማንን ሽጦ ይሆን? የሚሉ ጥያቄዎች ተነስተዋል። አድናቂዎቹ ለቀረበለት ጥያቄ ባልሄድስ? እናስ? ብሎ መልሶ ሲጠይቃቸው ያጨበጭባሉ፣ ሰው ራሱን እየሰደበ ነው ሲላቸው ያጨበጭባሉ፣ የሚሄድበት አቅጣጫ ጠፍቶት እንደተቸገረ ሲነግራቸው ያጨበጭባሉ፣ ተራራ ጫፍ ላይ ቁጭ ብዬ ሳስብ እውላለሁ ሲላቸው ያጨበጭባሉ፣ በተነፈሰ ቁጥር ያጨበጭባሉ፤ ዶክተሩ ምን ዓይነት ሰዎችን መርጦ አደራጅቷል? የሚያስብ አእምሮ የላቸውንም? ብለን ለመጠየቅ ተገደናል።

አዎን ዶክተር ብርሃኑ ነጋ በጭቃ ሹሞቹና በጭፍሮቹ አማካይነት በአገርና በሕዝብ ላይ ስለፈጸመው ደባ ዛፍም ላይ ወጥቶ ይሁን ተራራ ላይ፤ ዋሻ ውስጥም ሆነ ገዳም ገብቶ ናላውን የሚያዞር ሀሳብ ውስጥ እንደገባ ሊደብቀን አይችልም። ሌትም ቀንም ሲበላም ሲጠጣም ቁዘማ ባሕር ውስጥ ሰምጦ ነው።

በመአሕድና ቀጥሎም በመኢአድ ሥር ተደራጅተው ለቅንጅት በምርጫ ማሸነፍ ከፍተኛ እገዛ ያደረጉ የድጋፍ ድርጅቶችን በመከፋፈልና ተለጣፊ ቡድኖችን በማደራጀት ፓርቲው ትርምስና የእርስ በእርስ ንትርክ ውስጥ ገብቶ እንዲደካም ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ትልቅ የቤት ሥራ አከናውኗል። በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን በሚገባ ተረድቶታል። ከቶውንስ በውጭ አገር ከመኢአድ በስተቀር የትኛው ፓርቲ ነበር የድጋፍ ድርጅቶች የነበሩት? ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ያቋቋመው የቀስተ ደመና ፓርቲ እንኳን በውጭ አገር ይቅርና በአገር ቤትም ያለው አንድ ጽሕፈት ቤት የተውሶ ነበር። እንኳን የድጋፍ ድርጅቶችን ሊያቋቁም ቀርቶ ቀስተደመናም ተደራጅቶ የተጠናከረ ፓርቲ አልነበረም።

መሪዎቹ እሥር ላይ በነበሩ ጊዜ ዶክተር ብርሃኑ የሱን ቢጤዎች በማሳደም ሕዝብና የቅንጅት ፓርቲ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የመረጣቸውን መሪ በማግለል ራሱ ያልተመረጠ አምባገነን መሪ ለመሆን ትልቅ ፕላን ሲነድፍ ከርሟል። ከነበረከት ሰምዖን ጋር ባለው ልዩና ሚስጥራዊ ግንኙነት ከእሥር ቤት እየሾለከ ቤቱ ያድር እንደነበር፣ መጻሕፍት፣ አይፖድና የሚፈልጋቸው ነገሮች ይቀርቡለት እንደነበር፣ በውጭ አገር እሱን የሚደግፉ ድርጅቶች እንዲቋቋሙ ለማድረግ እነ በረከት ባዘጋጁለት በብርሃነ መዋና በአንዳርጋቸው ጽጌ አማካይነት በስሙ ለሚምሉ አድናቂዎቹና ጭፍራዎቹ ፕሬዚዴንቱ የማያውቁት መመሪያ ያስተላልፍ እንደነበር ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ታዛቢዎች በሰፊው ሲዘረዝሩ ሰንብተዋል።

የዴሞክራሲ ሥርዓት ባለበት በምዕራቡ ዓለም ለረጅም ዘመን ቢኖርም፣ መሪዎች በምርጫ እንደሚሾሙና እንደሚሻሩ የተመለከተ ቢሆንም፣ ስለዴሞክራሲና ነጻነት መጽሐፍ ደረሰ ቢባልም፣ ለተከታዮቹ ስለመልካም አስተዳደር ብዙ ዲስኩር ያደረገ ቢሆንም የዴሞራሲን ምንነትና አሠራሩን ከልቡ ተረድቶታል ለማለት አያስደፍርም:: “ግንድ በባሕር ውስጥ ቢበሰብስ ዓሣ አይሆንም” እንዲሉ ::

እርሱና ያሳደማቸው “መሪዎች” ከእሥር ይፈቱ ዘንድ ፎቶአቸውን ይዘን በፀሐይና በብርድ ስንጉላላ በነበርንበት ወቅት ለካስ ተከታዮቹ ዕውነተኛ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች የምንወድቅበትን መሰናክል ሲያዘጋጁልን ኖሯል::

በአንድ ወቅት ጠንካራ የወያኔ ተቃዋሚ መስሎ በኢትዮጵያ በቴሌቪዢን የታየው ዶክተር ብርሃኑ ለዴሞክራሲ ታጋይ ነው ብሎ ሕዝብ መርጦት ነበር:: የኋላ ታሪኩ በወቅቱ ብዙም አይታወቅም ስለነበር ታላቅ ሰው አገኘን ብሎ ሕዝብ መደሰቱ አልቀረም ነበር:: ዶክተሩ ሕዝብ የጣለበትን ዕምነትና አደራ እንደ ሸሚዙ አሽቀንጥሮ ጥሎ ሥራ ለማግኘት ተቸግሮ የኖረ ይመስል ሥራ አገኘሁ ብሎ አሜሪካ መኖርን መርጧል::

የሸረበው ገመድ ተብትቦ ጠልፎታል፤ የደከመበት የመሰሪ ዕድሞ የእምቧይ ካብ ሆኖበታል፤ የመረጠው ሕዝብ በባንዳነት ተግባሩ በጣም አዝኖበታል፤ እርሱን በመምረጡም ተጸጽቷል::

እነ ብርቱካንና ደበበ እሸቱን የመሳሰሉ ተከታዮቹን ያስማራበት ጉዳይ ግቡን አልመታም:: የፈረንሳይ ለጋሲዮን ነዋሪ የብርቱካንን የግል ሕይወትና ማንነት አውቋል:: ለምን ተግባር አመሻሽታ ወደ ቅንጅት እንደመጣች ሚስጥሩ ይፋ ሆኗል:: የሠፈሯ ነዋሪ ትግሉን ቀጥሏል:: ባንድ ወቅት “የቅንጅት ወርቅ” ተብላ አምስት ወጣቶች ለደህንነቷ ሲሉ ተሰውተዋል:: ዛሬ ብርቱካን ማንነቷ የተጋለጠ ስለሆነ ደፍራ በሰፈር ውስጥ አትታይም:: “ ብርቱኬ የቅንጅት ቡዳ” ተብላለች:: ኮበሌዋ ቤቷ ማደር እስከመተውና ጥላዋን እስከመፍራት ደርሳለች:: የምትፈራው ወያኔን አይደለም:: የፈረንሣይ ለጋሲዮን አካባቢ ነዋሪን ነው:: ከወያኔ ጋርማ አብራ ለመሥራት በቁርባን ተጋብቻለሁ ብላለች:: ሳትፋታ ከወያኔ ጋር ስትጋባ ወያኔ ፓርላማ ለመግባት ቅንጅት ያቀረባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች አንዳቸውንም አላነሳችም::

ዶክተሩና በየከተማው የተሰባሰቡ ጥቂት ጭፍራዎቹ ስለዴሞክራሲ ጉንጫቸው እስኪለፋ ያወራሉ፤ በተግባር ግን ሕዝብና ፓርቲው በዴሞክራሲያዊ መንገድ የመረጣቸውን የፓርቲውን መሪዎች በሸፍጥና በጩኸት ሊያወርዱ ይሞክራሉ፤ ስለግልጽነትና ተጠያቂነት ያወራሉ፣ በተግባር ግን ከመጋረጃ በስተኋላ ሴራና አድማ ሲሸርቡ ውለው ያድራሉ፤ ስለ መልካም አስተዳደር ይለፍፋሉ፣ ሥልጣን ቢኖራቸው ግን የጎጥ ፖለቲከኛነታቸው እንደሚያስፋፉ ተግባራቸው ይመሰክራል፤ አዲስ ባሕል አዲስ አሠራር እናመጣለን ይላሉ፣ በተግባር ግን የሚከረፉ ውሸት ሲነዙ፣ ሲያወናብዱ፥ ሲሸፍጡና የሚሠሩ ሰዎችን ሥም ሲያጠፉ ይውላሉ፣ ሌሎች ደክመው የሠሩትን ሲያበሻቅጡና ሲያጣጥሉ ይታያሉ:: ሀሰት መናገር የዶክተሩና ብርቱካን ዋና መለዮ ሆኗል:: አንዳርጋቸው ጽጌን አልሾምኩም ከሚለው የዶክተሩ ቅጥፈት አንስቶ የፖለቲካ እሥረኞች አንድ መቶ ብቻ ናቸው እስከሚለው የብርቱካን ውሸት እስካሁን የተደረደሩትን ውሸቶች ሁሉ መዘርዘር ይቻላል:: ተመዝግቦአልም:: እንግዲህ አገርንና ሕዝብን በሐቅና በዕውነት እንመራለን የሚሉት እነዚህ ናቸው::

ጥሩው ነገር የዶክተሩ ጭፍራዎች ንፋስ እንደመጣበት ደመና እየተበታተኑ ናቸው:: ያደረጉትን ስህተት በመረዳት አንዳንድ ግለሰቦች ወደ አንድነቱ ኃይል መምጣት ጀምረዋል:: እሰየው እንኳን ወደ ዕውነተኛው ትግል መጣችሁ እንላለን:: ገና ላልመጡትም የአንድነቱን ኃይል እንዲቀላቀሉ እናሳስባቸዋለን:: አንዳንዶቹ ደግሞ "ካፈርኩ አይመልሰኝ" ብለው የጥፋት መንገዱን ቀጥለውበታል:: ሌሎቹ ደግሞ ሁኔታውን እስካሁንም መገንዘብ አቅቷቸው መሀል ሰፋሪ የሆኑ አሉ:: የሚሠሩትን የሚያውቁና ተልዕኮው የተሰጣቸው ግለሰቦች ደግሞ ያልተረዱት ሌላ ነገር አለ:: አለቃቸው ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ውሃ ውስጥ እንደገባች አይጥ የሚሄድበትን አቅጣጫ ማወቅ ተስኖታል:: ሕዝብ ማንነቱን አውቆ ተፍቶታል:: መላወሻ የተቸገረ የድመት ዕውር ሆኗል:: የተረፉት ታማኝ ተከታዮቹ አንገቱ እንደተቆረጠ የእባብ ጅራት ቦታ እስኪጠባቸው ድርስ ይወራጫሉ:: ይራወጣሉ:: ጭንቅላቱ መቆረጡን እንዳላወቀው የእባብ ጅራት ናቸው:: በየከተማው የሚገኙ አድናቂዎቹ የሚገኙበት ሁኔታም ይኸው ነው::

በጭርቃ አስተሳሰባቸው ተገፋፍተው በሚያወጡት ጽሁፍ ከዳር እስከ ዳር ተጉዘው የኢትዮጵያን ሕዝብ አደራጅተው ለግንቦት 1997 ምርጫ ድል ለማስመዝገብ ያበቁትንና የሕዝብና የፓርተው ተመራጭ የሆኑትን ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልን ባልተገራ ምላሳቸው ተሳድበዋል፡፡ ለመሆኑ ከኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ጋር የሚወዳደር የትኛውን ሕዝብ የማደራጀት ሥራ አከናውነዋል? ከወያኔስ ጋር የት ቦታ ታግለዋል? ዕንቁራሪት በሬን አክላለሁ ብላ አብጣ ፈንድታ ሞተች እንዲሉ፡፡ በየከተማው የምንኖር ኢትዮጵያውያን እንቁራሪቶቹን ጠንቅቀን እናውቃቸዋለን፡፡ ለመማር፣ ለመሥራትና ራስን ለመቻል ዕድል ባለበት አገር የራሳቸውን የግል ኑሮ መምራት የተሳናቸው በ ethnic ghetto ውስጥ እየተራኮቱ የሚኖሩ፣ ለሥራ ህሞታቸው ተለቃልቆ የፈሰሰባቸው ደካሞች ናቸው፡፡ በድርጊታቸው የወያኔን አጀንዳ በማራመድ ለነመለስ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አበርክተዋል፡፡ ዛሬ ትግሉ ከወያኔ ጋር መሆን ሲገባው የእርስ በእርስ እንዲሆን አድርገውታል፡፡ የትግሉን አቅጣጫ ለማስቀየር ሞክረዋል፡፡

ዕውነተኛ የድጋፍ ድርጅቶች ሥራቸውን ለማከናን እንዳይችሉ ሕብረተ ሰቡን በማወናበድ መከፋፈልና ግራ በማጋባት መሰናክልና እንቅፋት መፍጠርን ዋና ተግባራቸው አድርገው ተያይዘውታል፡፡ ለዚህ ተግባራቸው ሥራ ማስፈጸሚያ መጠነ ሠፊ የወያኔ ድጋፍ አልተለያቸውም፡፡ የእንቅስቃሴአቸው ዋና ተጠቃሚ ወያኔ ነውና፡፡

እነዚህ ግለሰቦች ለዘመናት ትግሉን ያገዙ የድጋፍ ድርጅቶች መሪዎችንና አባላትን ይኮንናሉ፤ ገንዘብ በሉ፣ ዲክታተሮች ናቸው፣ ወዘተርፈ የሚሉ አሉባልታዎችን ያራግባሉ፡፡ የሀገርና የወገን ፍቅር የሚያቃጥላቸው የኢትዮጵያ ልጆች በወሬና በአሉባልታ እንደማይፈቱ አይገባቸውም፡፡ ጊዜና ገንዘባቸውን ቀርቶ ራሳቸውን ለመስዋዕትነት ያሰለፉ መሆናቸውን እነዚህ ለብርሀኑ ነጋ አድናቂነት የተሰባሰቡ ቀቢጸ ተስፈኞች አይገነዘቡም፡፡ ለመረዳትም የአስተሳሰብ አድማሳቸው ጠባብነት አይፈቅድላቸውም፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ የመረጣቸውን መሪዎቹን ያውቃል፡፡ ተወናብዶ የነበረውም የዳያስፖራ ኮሚኒቲ ዕውነቱ እየተገለጸለት ነው፡፡ ዶክተሩ ተራራ ጫፍ ላይ እስከመቼ ቁጢጥ ብሎ ተቀምጦ እንደሚቆይ ባይነግረንም ቁዘማውን አብቅቶ ከተራራው ላይ በሚወርድ ጊዜ -የሚወርድ ከሆነ? ሜዳው ገደል ሆኖ የሚቆምበት ምድር እንደማያገኝ አብሮ ሳያስብብት አይቀርም፡፡

የአንድነት ኃይሎች ይጠናከራሉ !
የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል!

የቅንጅት ሰሜን አሜሪካ ኢዲቶሪያል ቦርድ